# <u>የአቅም ግንባታ መምሪያ የ2001 ዓ.ም ዓመታዊ ሪፖረት</u>

## <u>መግቢያ</u>

የአገራችንን ህዝቦች  ከኋላቀርነትና ድህነት ህይወት በአጭር ጊዜ ዉስጥ በማላቀቅ መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ አገሮች ተርታ በማሰለፍ ህዝቡ ከልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንድሆን ለማስቻል በሚደረገዉ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ ልማትና መልካም አስተዳደር እንድሰፍን፤ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት እንድመዘገብና የዴሞክራስያዊ ሥርዓት እንድገነባ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ሥራዎች  ወሣኝ ሚና እንደሚጫወቱ  በማመን የአቅም ግንባታ ኘሮግራሞችን ቀጣይነትና ዘላቂነት ለማረጋገጥ በመልካም አስተዳደር ፓኬጆች ፣በሲቪል ሰርቪስ እና ፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራሞች በተለይም መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለዉጥ ትግበራ ላይ ትኩረት በመስጠት ሲንንቀሣቀስ  ቆይተናል ፡፡በዚህም መሠረት በለውጥ ፕሮግራሞች ፕሮጀክት ጥናትና ትግበራ ዋና የሥራ ሂደት እና የሌሎች የአቅም ግንባታ ሴክተር የሥራ ሂደቶች የ2001 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በቼክ ሊስት መሠረት በመከታተል እና በመገምገም ከዞን እስከ ቀበሌያት ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ እንደሚከተለው  አዘጋጅተን አቅርበናል፡፡

# I.የለውጥ ፕሮግራሞች ፕሮጀክት ጥናትና ትግበራ ዋና የሥራ ሂደት

## ሀ. <u>የመሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ/BPR/የሙሉ ትግበራ በተመለከተ</u>

1. እያንዳንዱ ሴክተር ወደ ሙሉ ትግበራ ከመግባቱ በፊት በትግበራ ወቅት የሚከናወኑ ዋና ዋና ትግበራት የግንኙነት ሥርዓት የለውጥ አመራር ስትራቴጂ እንዲሁም የክትትል ግምገማና ግብረ መልስ ሥርዓት የያዘ መርሃ ግብር ስለማዘጋጀታቸውና እየሰሩበት ስለመሆኑ፤
   - ወደ ሙሉ ትግበራ ከመግባታቸው በፊት ቢሮ ምቹ በማድረግ፤ አንድ የሥራ ሂደት በአንድ ክፍል ውስጥ እንድደራጅ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ተፈጥሮ ፍሰቱን ጠብቆ እንዲሰራበት በዞንና በወረዳ ሴክተር መ/ቤቶች ሁኔታ እንዲመቻች ተደርጓል፡፡
   - በደንብ ቁጥር 72/2001 ዓ.ም መሠረት በግልጽ በማወዳደር ሠራተኛው እንድመደብ ተደርጓል፡፡ከድልድሉ በኋላ የተመደቡ የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች እና ፈጻሚዎች አስፈላጊውን ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡በስልጠና መሠረት የ6 ወር ዕቅድ መርሃ ግብር ተክልሶ የክትትል ግምገማና ግብረ መልስ ሥርዓት በመዘርጋት  እየተሰረበት ነው፡፡
2. የሙሉ ትግበራ የተጀመረበት ቀን መቼ እንደሆነ
   - 6 ሴክተሮች ከጥር 1/2001 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሙሉ ትግበራ የገቡ ሲሆን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሴክተር ከመጋቢት 1/2001 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሙሉ ትግበራ ገብቷል፡፡

CAPACITY

3. የእያንዳንዱ የሥራ ሂደት ባሌበትና ፈጻሚዎች አንድ ላይ ሆነው የሙሉ ትግበራው በትክክል እየተካሄደ እንደምገኝ እንዲሁም በድርጊት መርሃ ግብሩ መሠረት ስለመጠናቀቁ ቼክ ሊስት አዘጋጅቶ ክትትልና ግምገማ ማድረጉ፤
   - እያንዳንዱ የሥራ ሂደት አስተባባሪና ፈጻሚ አንድ ላይ ሆኖ በቲም ሙሉ ትግበራውን በተቀናጀ ሁኔታ እየተተገበረ መሆኑ፣
   - የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅተው የክትትል ግምገማና ግብረ መልስ ሥርዓት በመዘርጋት ለውጡ በየመ/ቤቱ በስታንዳርዱ መሠረት ስለመጠናቀቁ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት በየደረጃ እየተሰራበት ነው፡፡
4. የሙሉ ትግበራ ሂደት ሲጀመር የሥራ ሂደቱ ባሌበትና ፈጻሚ ቲም አባላት አንድ ላይ ሆነው ተገቢውን ግበዓት ማሰባሰቢያ ቅጽ ማዘጋጀታቸውን፤
   - የሥራ ሂደት አስተባባሪዎችና ፈጻሚዎች በቲም አንድ ላይ ሆኖ ተገቢውን ግበዓት በማሰባሰብ የተለያዩ ቅጻቅጾችን በመጠቀም እየተሰራበት ነው፡፡
5. በየሥራ ሂደቱ የትግበራ ማኑዋልና ቲም ቻርተር ላይ ስልጠና ሳይወስዱ የተካተቱ ሠራተኞች ስለመኖር አለመኖር ካሉ መሠረታዊ ምክንያቱ ምን እንዲሆን፤
   - በየሥራ ሂደቱ የትግበራ ማኑዋልና ቲም ቻርተር በክልሉና በዞኑ አማካኝነት ስልጠና በማገኘት ሁሉም ወደ አዲሱ ሥራ ሂደት ገብቷል፡፡ ሆኖም በተሰበሰበው መረጃ መሠረት የተወሰኑ ሠራተኞች በግብረ ሃይል እና ከኋላም ተሻሽሎ በተላለፉ መመሪያዎች መሠረት የተዳደሉና አዲስ የተቀጠሩት ስልጠና አለገኙም፡፡
6. በሴክተሩ የለውጥ ተቃዉሞ አያያዝና አመራር ላይ ስልት ነድፎ የመስራቱ ሁኔታ በምን ደረጃ ላይ እንደምገኝና የተደረጉ ጥረቶች ምን እንደሚመስሉ፤
   - የለውጡ ተቃውሞ አያያዝና አመራር በየደረጃ ስልት ነድፎ ሴክተሮች ውይይት በማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ አሠራር ሥርኣት ዘርግተው እየሠሩበት ይገኛሉ፡፡
7. የሥራ ሂደት ባሌበት እና የሥራ ሂደት አስተባባሪ አመዳደብ ምን እንደሚመስል በዚህ ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችና የተሰጡ መፍትሄዎች
   - የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች በደንብ ቁጥር 72/2001 መሠረት በምደባ እና በሹመት ከዞን እስከ ወረዳ ድልድል ተካሂዷል፡፡ በሶስት የሥራ ሂደቶች በሹመትና በሌላም ምክንያት አስተባባሪዎች በመልቀቃቸው ብቃትን መሠረት በማድረግ ወዲያውኑ ተተክቷል፡፡
8. በድልድሉ ደንብ ላይ የተዘረዘሩትን የድልድል መስፈርቶች መሠረት በማድረግ ሠራተኞችን በግልጽ አወዳድሮ መመደብ፤
   - በድልድሉ ደንብ ላይ በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሠረት በማድረግ በሁሉም ሴክተሮች ከዞን እስከ ወረዳ ግልጽ በሆነ መንገድ ሠራተኛው ተወዳደሮ ተመድቧል፡፡
9. የሰው ኃይል አመዳደብ ላይ የታዩ ክፍተቶች የተነሱ ቅሬታዎችና ዓይነታቸው፤
   - የታዩ ክፍተቶች የሉም

CAPACITY

10. የሥራ ሂደቱና በውስጡ የያዛቸው ሠራተኞች ተገቢነት/የሙያ መስመር የትምህርት ደረጃ አገልግሎትና በሌሎች መስፈርቶች ሲታይ/፤

➢ እያንዳንዱ ሥራ ሂደት በውስጡ የያዛቸው የሥራ ሂደት አስተባባዎችና ፈጻሚዎች የትምህርት ደረጃ፣ የሙያ መስመርና አገልግሎት መስፈርቶች ሲታይ ደንቡን የተከተለ እና ፍትሓዊ መሆኑን በየደረጃውእስከ ወረዳዎች በቼክ ሊስት መሠረት ክትትል ተደርጓል፡፡

11. በሥራ ሂደቱ ላይ ተወዳድረው ሳያልፉ ወይም ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ በውድድር ካሸነፉ ሰራተኞች ጋር የተቀላቀሉ ሠራተኞች ስለመኖራቸው፤

➢ የለም

12. በየደረጃው ያለ የድልድል ኮሚቴው አወቃቀርና ስብጥር የድልድል ደንብን ተከትሎ ስለመሆኑ፤

➢ በዞን ሴክተሮችና በወረዳዎች የድልድል ኮሚቴዎች እንደየመ/ቤቶች የሰው ኃይል ብዛት ማለትም ከ5-10 በሚደርሱ ኮሚቴዎች አወቃቀርና ስብጥር በተቀመጠው መመሪያ መሠረት የውድድር የጊዜ ሰለዳ በማውጣት ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ባለው አኳኋን ተከናውኗል፡፡

13. በድልድሉ የታቀፉ ሠራተኞች አዲሱ የሥራ ምደባ ደብዳቤ ላይ የሥራ መደብ መጠሪያና የወር ደመወዝ መጠን ብቻ እንዲገለጽላቸው ስለመደረጉ፤

➢ በድልድሉ የታቀፉ ሠራተኞች አዲሱ የሥራ መደባ ደብዳቤ ላይ የሥራ መደብ መጠሪያና የወር ደመወዛቸው ብቻ እንዲገለጽ ተደርጓል፡፡በየደረጃም ክትትልና እገዛ ተደርጓል፡፡

14. በድልድሉ ምን ያህል ሠራተኞች እንደታቀፉ ምን ያህል ሠራተኞች እንዳልታቀፉ፤

➢ በድልድሉ ያልታቀፉ ሠራተኞች 234 ሲሆን የታቀፉ ሠራተኞች ብዛታቸው 583 ነው፡፡

15. በምደባ ካልታቀፉት ውስጥ ምን ያህል 50 እና በላይ እንዳመጡ ምን ያህሉ ከዚህ በታች እንደሆኑ፤

➢ በዞኑ 4 ሠራተኞች ከ50% በታች በማምጣት ያልተደለደሉ መሆናቸው እና ሌሎች ከ50% በላይ ቢያመጡም በትምህርት ዝግጅት ማነስ ምክንያት አልተደለደሉም

16. ለየሥራ ሂደቶቹ የቢሮዎች ዝግጅትና አቀማመጥ ለስራው ያለው ምቹነትን በተመለከተ የውስጥ አደረጃጀታቸው ስለማሟላቱ የሥራ ክፍሎቹ ስፋት የክፍሉ ችግር ባለባቸው ቦታዎች የኃላፊዎች ክፍልና የመሰባሰቢያ አደራሾች ለዚህ ተግባር እንዲውሉ መደረጋቸው ይህ በሌለበት ጊዜያዊ የመስሪያ ቦታ ስለመመቻቸቱ፤

➢ የቢሮ ዝግጅትና አቀማመጥ ለመሰረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ ምቹ ከማድረግ አኳያ ግርግዳን በማፍረስ አንድ ሥራ ሂደት በተሻለ መጠን በአንድ ቢሮ ውስጥ ሆኖ እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም መ/ቤቶችን እንደየሥራ ሂደቶቻቸው ስፋት ቢሮ የመቀያየርም ሥራ ተሠርቷል፡፡

CAPACITY

17. ትግበራውን የተሳካ ለማድረግ ለየሥራ ሂደቶቹ የሚያስፈጉና በሴክተሩ በኩል የተደረጉ የቁሳቁሶችና መሣሪዎች አቅርቦትና አደረጃት/በግዥም ሆነ ከየአስተዳደር እርከኑ በማሰባሰብ በኩል/ ምን እንደምመስል፤

➢ሙሉ ትግበራውን የተሳካ ለማድረግ ለሥራ ሂደቶች ቁሳቁሶችና መሣሪያዎች አቅርቦትና አደረጃጀት ከለው በጀት ቢሮ ምቹ ከማድረግ /በግዥም ሆነ ከየአስተዳደር እርከኑ በማሰባሰብ በኩል/ በየደረጃ ብርቱ ጥረት ተደርጓል፡፡

18. የሥራ ሂደቶች የተጠኑትና የሚተገበሩበት በሴክተር ደረጃ ከመሆኑ ጋር ተያየዞ ሴክተሮች ለየሥራ ሂደቶች ያደረጉት የበጀት ድጋፍ ምን እንደሚመስለ፤

➢በሴክተር ደረጃ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሴክተሮች ለየሥራ ሂደታቸው ያደረጉት የበጀት ድጋፍ አበረታች ቢሆንም ወጥነት ይጎለዋል፤

19. በየሥራ ሂደቶች ባሌበት/አስተባባሪና በፈጻሚዎች መካከል ያለው ግንኙነት ምን እንደምመስል በተለይም በትግበራ ሂደት እየተፈጠሩ ያሉ አዳዲስ እሴቶች ማለትም የቲም ስሜት/team spirit/ ተግቶና ተተካክቶ የመስራት ልምድ የአገልጋይነት ስሜት እየተፈተረ ስለመሆኑ፤

➢በየሥራ ሂደቶች በአስተባባሪና በፈጻሚዎች መካከል ያለው ግንኙነት መልካም መሆኑን የቲም ስሜት የሚበረታታ መሆኑና ፈጻሚዎች እስከ መጨረሻ ወስኖ የሰሩ መሆናቸው

➢የቲም ስሜት ፈጥሮ ተተክቶ ከመሥራት አኳያ በወረዳ ደረጃ በተለይ በኛንጋቶም ወረዳ ክፍተት ይታያል፡፡የሥራ ሂደቶች ሲጀምሩ የሰው ኃይላቸው ባልተሟላበትና አንዳንዱ አስተባባሪ ብቻቸውን ሆነው እየሰሩ መሆናቸው፣

20. እያንዳንዱ ክልል መሰሪያ ቤት ደጋፊ የሥራ ሂደቶች ከራሱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማጣጣሙ ሥራ በማጠናቀቅ ወደ ታችኛው እረከን ማስተላለፍ እና በየደረጃው ተግባራዊ መደረጉ፤

➢እያንዳንዱ ክልል መ/ቤት ደጋፍ የሥራ ሂደቶች ከራሱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማጣጣሙ ሥራ ማጠናቀቁና የማስተላለፍ እንዲሁም ተግባራዊ የማድረግ ሁኔታ አበረታች መሆኑን

21. የደጋፊ የሥራ ሂደቶችን ለመከታተል የሚያስችል አደረጃጀት መኖሩ ማለትም ከተጠናበት ሴክተር ወደ ሚተገበርበት ሴክተር ይህንን ለመከታተል የሚያስችል ሁኔታ ስለመፈጠሩና የአፈጻጸም ስለመቀየሱ፤

➢ደጋፊ ሥራ ሂደቶችን ከመደገፍ እና ከመከታተል አኳያ ያለው አደረጃጀት መኖሩ ማለትም ከተጠናበት ሴክተር ወደ ሚተገበርበት ሴክተር ለመከታተል የሚያስችልበት አሠራር ተፈጥሮአል፡፡በተለይ በፋይናንስ እና ኢኮኖሚ የተጠናው የልማት ዕቅድ በየሰክተር መ/ቤቶች እንዲተገበር ሥልጠና በመስጠት ጭምር ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡

22. የጥናት ሰነዱ ውድቅ ያደረገቸው ህጎችና አስተሳሳቦች ቀርተው በአዲስ መልክ የተቀረጹ አስተሳሳቦችና በተተኪነት የታሰቡ ህጎች ተፈጻሚ ስለመሆናቸው፤

➢የጥናት ሰነድ ውድቅ ያደረጋቸው ህጎች እና አስተሳሰቦች ቀርተው በአዲስ መልክ በተቀረጹ አስተሳሰቦች እና ህጎች በተተኪነት ተፈጻሚ እንዲሆኑ እየተደረገ ሲሆን የሚመለከታቸው

CAPACITY

ክፍሎች እና ባሌድርሻ አካላት እንዲያውቁ ስታንዳርዶች በግልጽ ቦታ ተለጥፎ  አዲሱ አሠራር ተፈጻሚ እየሆነ ነው፡፡

23. በየደረጃ የሚገኙ አስፈጻሚ አካላት በተሰጣቸው ተግባርና ዓላፊነት መሠረት ክትትልና ግምገማ ስለመደረጋቸው፤

➢በየደረጃ የሚገኙ አካላት የየቀናትና የሳምንታት መከታተያ ፎርሞችን በመጠቀም፤ቼክ ሊስት በማዘጋጀት፤ውይይቶች በማካሄድ ክትትልና ግምገማ  እየተሰራበት መሆኑን፤

24. በየሴክተሩ ያሉ ኃላፊዎች የህዝብ ግንኙነት ክፍሎች የየሴክተራቸውን የሥራ ሂደቶች አስተባባሪና አጠቃላይ ሁኔታ መረጃዎችን ለህዝብ ከማስተዋወቅ አኳያ እያከናወኑት ያለው ተግባር ምን እንደምመስል፤

➢በየደረጃ ያሉ ሥራ ሂደት አስተባባሪዎች የሥራ ሂደታቸውን ከማስተዋወቅ/በዞን ደረጃ በተለይ በዞን አቅም ግንባታ መምሪያ ለኤፍ.ኤም.100.9 ጋዘጠኞች አጠቃላይ በአዲሱ አሠራር ሥራ ሂደት ለውጥ  ላይ መግለጫ ተሰጥቷል፡፡በዞን ሴክተሮች እና በወረዳዎች ሥራ ሂደታቸውን ለማስተዋወቅ ቢሮሸሮችን የማዘጋጀት ልምድ እየዳበረ መጥቷል ፡፡

25. በእያንዳንዱ ሴክተር ውስጥ ለውጡን ሊሸከሙና ሊያራምዱ የሚችሉ የለውጥ ኃይሎች ስለማፍራታቸውና መበራከታቸው፤

➢በተዘረጋ አሠራር ለውጡን ሊሸከሙና ሊያራመዱ የሚችሉ የለውጥ ኃይሎች እያፈሩና ለመሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ እንደሥርዓት እንዲተከል እየተሠራበት መሆኑን፣

26. የሥራ ሂደቱ አፈጻጸም ከተደራሽ ግቦች አንጻር/ከመጠን፣ከጊዜ፣ከጥራት፣ከወጪ/እየተሳካ ስለመሆኑ ያልተሳካ  በጥረት ተደራሽ ግብ ካለ መሠረታዊ ምክንያቱ፤

➢በእያንዳንዱ ሥራ ሂደት ከዞን እስከ ወረዳ ከተደራሽ ግቦች አንጻር/ከጊዜ፣ከመጠን፣ ከጥራት፣ከወጪ/ተከፋፍሎ ከሥራ ሂደት አስተባባሪ እስከ ፈጻሚ ድረስ እየተሰራበት መሆኑና የተሳካ ቢሆንም በአንዳንድ መ/ቤቶች ከሰው ኃይል እጥረት የተነሳ በተሟላ ሁኔታ ግቦች የተሳካ  ነው ማለት በዞናችን በተለይ በወረዳዎች አካባቢ  ያስቸግራል፡፡

27. የተገኙ አዳዲስ ተቋማት ባህልና አስተሳሰቦች ፣ አጠቃላይ የለውጥ ውጤቶች፤

➢አዲስ ተቋማዊ ባህልና አስተሳሰቦች ከለውጡ አንጻር የቲም አሠራር እና ፈጻሚዎች ወስኖ እስከ መጨረሻ ሥራውን ቆርጦ የመሥራት ሁኔታ በአዲሱ ካገኘናቸው ተቋማዊ ባህልና አሠራር ተገልጋይ ተኮር መሆኑ መልካም ውጤት የታየበት ነው፡፡

በአጠቃላይ መሠረታዊ አሠራር ሥራ ሂደት ለውጥ/BPR/ወደ ሙሉ ትግበራ ከተገባ በኋላ

በተደረገው ግምገማ አበረታች ውጤት ተገኝቷል፡፡ከነዚህም ውስጥ

- የሰው ኃይል እና የቢሮ አደረጃጀት ለአገልግሎት አሰጣጥ ምቹ ሆኖ በመደራጀቱ ተገልጋዮች ውጣ ውረድ ሳይበዛ አገልግሎት ከአንድ ቦታ ብቻ ማግኘት መቻላቸው ፤ ፈጻሚዎች የሚሰጡትን አገልግሎት በኃላፊነት  እና በተጠያቂነት መንፈስ የመ/ቤት

CAPACITY

ኃላፊን ሳይጠብቁ ከጫፍ እስከ ጫፍ መፈጸም እና መወሰን በመቻላቸው የተገልጋይ መጉላላት መቀነሱ፤ፈጻሚዎች ከግል ውጤት ይልቅ ለተቋም ውጤት ትኩረት በመስጠት የጋራ/የቲም/ ስሜትና መንፈስ መፈጠሩ፤የሥራ ጊዜን ከመጠቀምና ለተገልጋዮች የሚሰጥ አገልግሎትና መረጃ ላይ ለማሻሻል መታየቱ በምሳሌነት የሚጠቀስ ንግድ ኢንዱስትሪ ፣ፋ/ኢ/ልማት እንዲሁም ፖሊስ ሴክተር መ/ቤቶች ከዞን እስከ ቀበሌ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ ማስመዘገብ የጀመሩ ተቋማት መሆናቸውን በግምገማ ተረጋግጧል፡፡

## ለ.የገጠር ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ አፈጻጸም በተመለከተ

## የመልካም አስተዳደር መርህ መሠረት በማድረግ የሚታዩ ዝርዝር ጉዳዮች

<u>ዲሞክራሲያዊ አሠራርን በተመለከተ</u>

1. ህዝቡን በግልም ሆኖ በጋራ የሚያከናዉናቸውን ተግባራት አምኖ ብቻ እንዲፈጸም ከማድረግ አኳያ ያለው ጥረት ምን ይመስላል? የቀበሌ መዋቅራችን በግንባር ቀደም አርሶ አደር እየተመራ ነው?
   - ህዝቡን በግልም ሆነ በጋራ የሚያከናዉናቸውን ትግባራት አምኖ ብቻ እንዲፈጽም ከማድረግ አኳያ ያለው ጥረት በየደረጃ በተሰጠ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ህብረተሰቡ አምኖ ብቻ እንዲሠራ ስለአደረገ አመራሩም የሚፈለገውን ለውጥ ለማምጣት ከማሳመን በስተቀር አማራጭ እና አቋራጭ መንገድ እንደሌለ አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ አስገድጎ ማሰራት እንደነውር እየተቆጠረ ነው ፡፡ቀበሌያት መዋቅራቸው በግንባር ቀደም አርሶ አደርና አርብቶ አደር እየተመራ ነው፣
2. ህብረተሰቡን አሳምኖ የልማት ዕቅዶችን በቅንጅት ከአፈጻጸም አንጻር የተዘረጋ የአሠራርና የአደረጃጀት ሥርዓት ምንድነው?
   - ህብረተሰቡን አሳምኖ የልማት ዕቅዶችን በቅንጅት ከማስተባበር አንጻር የሚሰራቸው ዕቅዶች ሲወጡ ችግሮቹንና ፍላጎቶቹን በመለየት በሰፊው ተሳትፎ አሰራር ሥርዓቶች ተዘርግቷል፡፡ይኸውም  የኢንስፔክሽን አሠራሮች በየደረጃ የተዘረጋ አሠራርና አደረጃጀት ሥርዓት መኖሩ፣እንዲሁም በአደረጃጀት ላይ በቀበሌያት  እና በመንደር የልማት ቡድን፣ የጤና፣የትምህርት፣ግብርና መዋቀሮች በመጠቀም የአሠራር ሥርዓት እስከ ታችኛው መዋቀር እንዲዘረጋ ተደርጓል፡፡
3. ህዝቡን አሳምኖ ወደ ልማት ለማስተባበር በማስገባት በተግባር በማሳየት የማያቋርጥ ተሳትፎ እንዲኖርና ሞደል በመጠቀም የማሳመን አሠራር በምን ደረጃ ይገኛል?
   - ህዝቡን አሳምኖ ወደ ልማት በማስተባበር በማስገባት በተግባር በማሳየት የማያቋርጥ ተሳትፎ እንዲኖርና ሞዴል በመጠቀም የማሳመን አሠራር በየደረጃ ተዘርግቶ እየተሰራበት ነው፣አምኖ እንዲተገበር ማለት አብዛኛውን ነገር በመተግበር የሚያዩበት ሁኔታ ተመቻችቶ እየተስፋፋ ነው፡፡

CAPACITY

4. ሞዴል ግለሰብና መንደር በፓኬጅ ላይ በተቀመጠው አጠቃላይና ዝርዝር መሥፈርት መሠረት ለመለየትና ለመፍጠር የተደረገው ጥረትና ቅንጅታዊ አሠራር ምን ይመስላል?/ከግብርና ገጠር ልማት፣ከጤና፣ከትምህርትና ከፍትህና አስተዳደር አካላት ጋር/

❖ ፓኬጁን ለማስፈጸም በአብዛኛው ቀበሌያት አጠቃላይ ዝርዝር መስፈርት መሠረት ለመለየት እና ለመፍጠር በአብዛኛው ቀበሌያት ጥረት በማድረግ ቅንጅታዊ አሠራር ተዘርግቶ ሞዴል ግለሰብ እና መንደር ተቀምሮሃል።በተለይ ከግብርና ገጠር ልማት፣ከጤና እና ከትምህርት አንጻር የተዘረዘሩ መስፈርቶችን በመጠቀም ሞዴሎችን በመለየት እየተሰሩ ነው።

4. በወረዳ ደረጃ ምን ያህል ሞዴል ቀበሌ፣መንደርና ግለሰብ በመፍጠር ተግባር ላይ ለማዋል ተችሏል?

CAPACITY

የዞኑ ስም፡- <u>ደቡብ ኦሞ ዞን</u>

| ተ.ቁ | ሞዴል ቀበሌ የሚገኝበት ወረዳ ስም | በወረዳው ጠቅላላ ቀበሌ ብዛት | ሞዴል ቀበሌ ብዛት በቁጥር | ሞዴል መንደር ብዛት በቁጥር | ሞዴል ግለሰብ ብዛት በቁጥር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | ጂንካ ከተማ አስ/ር | 3 | 1 | 1 | - | - | - |
| 2 | ማሌ ወረዳ | 22 | 11 | 27 | - | - | 220 |
| 3 | ሐመር ወረዳ | 38 | 15 | 27 | - | - | 81 |
| 4 | ኛንጋቶም ወረዳ | 20 | 5 | - | - | - | - |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ደቡብ አሪ ወረዳ | 48 | 5 | 20 | 42 | | 42 |
| 6 | ሰሜን አሪ ወረዳ | 33 | 4 | 4 | 38 | 1 | 39 |
| 7 | በና ፀማይ ወረዳ | 28 | 5 | 15 | 20 | 5 | 25 |
| 8 | ዳሰነች ወረዳ | 40 | 3 | - | 3 | 1 | 4 |
| 9 | ሳላማጎ ወረዳ | 21 | 4 | 3 | 4 | - | 4 |

5. ይህ ጥረት የልማት እንቅስቃሴያችንን ከመደገፍና ኅ/ቡን ለልማት ሥራ ከማነሳሳት አንጻር ምን አስተዋጾ አድርጓል?
   - ❖ የልማት እንቅስቃሴዎችን ከመደገፍ እና ህብረተሰቡን ለልማት ከማነሳሳት አንጻር በየደረጃ በተለይ በአርሶ አደሩ ውስጥ የተነሳሽነት እና የተፎካካሪነት የለውጥ ስሜት ፈጥሮሃል፡፡
6. ሞዴል በመጠቀምና ያልተቋረጠ ተሳትፎን ተግባራዊ በማድረግ በባለፉት ሶስት አመታት ዓመታዊ የወረዳና የቀበሌ የዕቅድ አፈጻጸማቹ በምን ያህል ፐርሰንት እያደገ መጥቷል?
   - ❖ ሞዴል በመጠቀም እና ያልተቋረጠ ተሳትፎን በማድረግ የወረዳ እና የቀበሌያት የዕቅድ አሠራር በሁሉም ቀበሌያት ተዘርግቶ አበረታች መሆኑ የሚያሳይ ምልክቶች ታይቷል፡፡ሞዴሎችን በማሳየት በርካታ አርብቶ አደሮች ለሥራ መነሣሣታቸው እና የግል ኑሮሃቸው እንዲሁም የጋራ ልማት ዙሪያ ለውጥ ማምጣታቸው/ በና ፀማይ እና በሐመር ወረዳ/
7. ሞዴል እንዴት ነው የምንጠቀመው? በሞዴል መጠቀም የተገኙ ውጤቶችን በተመለከተ አንድ ቀበሌ ከአንዱ ቀበሌ፤አንድ መንደር ከአንዱ መንደር ልምድ እንዲለዋወጡ ያለው የመማሪያ መድረክ ዝግጅትና አሠራር ምን ይመስላል?
   - ❖ ሞዴል የምንጠቀመው በሁለት መንግድ ነው፡፡

     1ኛ ሞዴል ግለሰቡን ወይም መንደሮችን እና ቀበሌያት መጥተው በአካል እንዲያዩ በማድረግ

     2ኛ ሞዴል የሆኑት ወደ ሌሎቹ ሄደው ሌሎች ጀማሪዎች የሚሰሩትን እያዩ ከራሳቸው ልምድ ተነስተው እንድማሩ በማድረግ ሞዴሎችን እንጠቀማለን

     ሞዴል በመቀመር እና በማስፋፋት የተገኘ ውጤት ለማስፋፋት ከቀበሌ ወደ ቀበሌ ፤ከመንደር ወደ መንደር፤የመማሪያ መድረክ ተዘጋጅቶ በየደረጃ

CAPACITY

እየተሰራበት ነው እንዲሁም የጉብኝት ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ሞዴል በየደረጃ ባለድርሻ አካላት እንዲጠቀሙ እየተደረገ ይገኛል፡፡

8. ሞዴል መገንቢያ ማበረታቻና ኪሳራ ማካካሻ ሥርዓት ለመዘርጋት የተደረገው ጥረት ምን ይመስላል? ሞዴል ግለሰብና መንደር/ቀበሌ/ ተቋም ለመፍጠር የተዘረጋው ሥርዓት በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል?
   - ❖ በዚህ ዙሪያ በየደረጃው ለሽልማት የልማት አርበኞች ሲመለመሉ ትኩረት የሚደረገው በነዚህ ሞዴሎች ላይ ሲሆን ከዚህ የተለየ አሠራር የተዘረገ የለም

**በጋራ መግባባትና ተሳትፎን በተመለከተ**

9.ህዝቡን በግልና በጋራ ሥራው ከማቀድ ጀምሮ እስከ ፍጻሜውና ውጤቱን እስከ መገምገም የሚዘልቅ ሰፊ የህዝብ ተሳትፎ አሠራር ከመዘርጋት አኳያ ያለው ሂደት ምን ይመስላል?
   - ❖ በአርብቶ አደር እና በአርሶ አደር ወረዳዎች ህብረተሰቡ ዕቅዶችን አንብቦ ለመረዳት ክፍተት ቢኖርም በባለሙያዎች የሚዘጋጁ ዕቅዶች በአስተርጓሚ ተተርጉሞላቸው እንዲረዱና መጨመር ያለበትና መቀነስ ያለበት ነገር ካለ ተነጋግሮ በጋራ መግባባት የዕቅድ ሥራ ላይ ከዝግጅት እስከ ትግበራና ግምገማ ድረስ ተሳታፊ የሚሆኑበት አሰራር ተዘርግቶ እየተሰራበት ነው፡፡

10. ተሳትፎው በዋነኛነት በግል ሥራ ላይ ያተኩረ እንዲሆን /20/ ለጋራና 80 ለግል ያለውን አሠራር ለመተግበር/ የተደረጉ ጥረቶች ምን ይመስላል? በተጨማሪም በጋራ ሥራ ተሳትፎን ያለማቋራጥ ለማረጋገጥና ተግባራዊ ለማድረግ ያለው አሠራር በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?
   - ❖ በተሰጠ ስልጠና ህዝቡ በጋራ ሥራዎች እና ችግሮችን በጋራ ከመለየት ጀምሮ ለችግሮቹ ቅድም ተከተል በመስጠት ከማቀድ እስከ መተግበር እንዲሁም እስከ መገምገም የሚሠራ ሲሆን በግል ሥራዎችም ከምደገፈው አካል ጋር በማስማማት ዕቅድ አቅዶ በዕቅድ እየተሰራ መሆኑን

11. የተሳትፎው መደረክ በሰፋት በመፍጠር ከስብሰባ በለፈ ህዝቡ በፖለቲካዊ፣በኢኮኖሚያዊ እና በማህነበራዊ ሁኔታዋች ላይ በራሱ መድረክ ፈጥሮ ተሳትፎውን የሚገልጽበት አሠራር ተዘርግቷል ወይ ?አብነት ይጠቀስ
   - ❖ በተዘረጋ አሠራርና በየደረጃ በተሰጠ ስልጠና የተሳትፎሃዊ መድረክ በስፋት እየተፈጠረ መሆኑን ለአብነት በአብዛኛው ወረዳ/በኛንጋቶም፣ደቡብ አሪ፣ማሌ፣ሐመር ወረዳዎች በልማት ቡድን በሴል፣በዕድር፣በዕቁብ፣በሠላም፣በማህበራዊና በፖሊቲካዊ ጉዳዮች ላይ የመወያየት ልምድና ባህል ከመተከሉ ባሻገር በየመንደሩ በልማት ቡድንና በሴል በተዋቀረው አደረጃጀት በመጠቀም የዕለት ዕለት ውሎዋቸውን የሚለዋወጡትና የሚናገሩበት ምቹ ሁኔታ አለ፣

CAPACITY

12. በልማት ዕቅድና ውሳኔዎች ላይ ህዝቡን ማሳተፍ የሚያስችል አሠራር መዘርጋትና የጋራ መግባባት መፍጠር ሁለንተናዊ ተሳትፎ የማረጋገጥ ሥራ እየተሰራ ነው ወይ? አብነት ይተቀስ

- ❖ በጋራ በቀበሌያት ደረጃ ሥራዎች ለመሥራት የሚወርድ ዕቅዶችን እንደ አካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ ዕቅዱን በመከለስና ዕቅዱ ያነስ ከሆነ ከአቅም በታች ከሆነ የሚጨምሩበት ሁኔታ እንዳለና የአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ ከሆነ የሚቀነስበት ሁኔታ መኖሩ

13. በዕቅድ አፈጻጸም ክትትል ግምገማ ላይ ተጠቃሚ ህብረተሰቡን ማሳተፍ የሚያስችል አሠራር ተዘርግቷል ወይ? አብነት ይጠቀስ? በወረዳቹ ምን ያህል የኢንስፔክሽን ቡድን አሠራር በተጠናከረ መልኩ በቀበሌ ደረጃ ተዘርግቷል?

- ❖ በዕቅድ አፈጻጸም ላይ ክትትል እና ግምገማ በማድረግ ተጠቃሚ ህብረተሰቡን በማሳተፍ ቋሚ ኮሚቴ በማቋቋም በቀበሌ ደረጃ በየወቅቱ ከአሰብ ጀምሮ እስከ ውጤት ድረስ በጋራ ህብረተሰቡን በማሳተፍ የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቷል። ለአብነት
  1. ባላ፣ኮይቤ፣ጉዶ ቀበሌያት በማሌ ወረዳ፤
  2. ላላ፣ሽንቆ፣በሽዳ እና ደንባይቴ ቀበሌያት በሐመር ወረዳ

14. በተግባሮቻችን ዙሪያ በየደረጃ ያለውን ባለሙያ በብቃት ማሳተፍ የሚያስችል አሠራር መዘርጋትና ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር የተገኙ ውጤቶች ምን ይመስላል?

- ❖ በተግባሮቻችን ዙሪያ ህብረተሰቡ፣ባለሙያ እና ሱፐርቫይዘሮች ጋር በጋራ በመወያየት በብቃት ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ በተለይ ባለሙያ ማሳተፍ የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት በቀበሌያት ደረጃ ባለሙያዎች ሥራዎችን አቀናጅተው በመሥራታቸው ህብረተሰቡ መብትና ግዴታ ላይ ያለው ግንዛቤ ማደጉ፣

15. የቀበሌ ምክር ቤት ማጠናከርና የብዙሃን ማህበራትን ተሳትፎ መሠረት በማድረግ በአካባቢ የልማት ጉዳይ በቀበሌ ምክር ቤት እንዲወያዩ ያለው አሠራርና የተገኙ ውጤቶች ምን ይመስላል?

- ❖ የቀበሌ ምክር ቤት በአብዛኛው በወር አንዴ እንዲወያዩ እና ያለው ውይይታቸውም በአካባቢው ልማት ጉዳዮች እና ችግሮች ዙሪያ ሲሆን በት/ት፣በጤና፣ግብርና መልካም አስተዳደር የተገኙ ውጤተቶች አሉ።

## ቶሎ ምላሽ መስጠት

16. ለህዝብ በጋራ በሚያነሳቸው ጉዳዮች ቶሎ ምላሽ ለመስጠት ያለው አሠራር ምን ይመስላል?

- ❖ በየደረጃ በመልካም አስተዳደር ላይ በተሰጠ ስልጠና ህብረተሰቡ በጋራ በሚያነሳቸው ጉዳዮች ወቅታዊ ምላሽ ለሚያስፈል ጉዳዮችን በጥሞና ሰምቶ መፍትሄ የመስጠት አሰራር በሁሉም ወረዳ ተዘርግቷል።በተጨማሪም ፈጣን ምላሽ የሚያስፈልግ ሆኖ ሊሰጥ ያልቻለበትን ምክንያት በማስረዳት ግንዛቤ በማሳደግ ህብረተሰቡ በጋራ ጉዳይ ላይ የጋራ አቋም እንዲይዝ ይደረጋል።

CAPACITY

17. ባለጉዳይን በቀጠሮ የማመላለስ አሠራር እንዳይኖር በማድረግ ባለጉዳይ ሳይጉላላ ፈጥኖ ምላሽ የሚሰጥበት አሠራር ምን ይመስላል?

- ❖ በላጉዳይ በቀጠሮ እንዳይመላለስ በተዘረጋ አሠራር ፈጣን ምላሽ የሚሰጥበት ተመቻችቷል፡ ፡ይኸውም ጉዳይ ተቀባይ በሁሉም ቀበሌያት በመዘርጋት እንዲሁም አገልግሎት ፈላጊው አገልግሎቱን ለማግኘት ቅድመ ሁኔታ ዝርዝሮች በመለጠፍ የባለጉዳይ ተጨባጭ ችግር እንደ ራስ ችግር በማየት እና በመጨነቅ በወቅቱ ምላሽ በመስጠት ያለው ጅምር ሥራ አበረታች ነው፡፡

18. በትክክልም ሆነ በስህተት ቅሬታ ያደረበት ዜጋ ወዲያው ቅሬታውን የሚያሰማበት የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቷል ወይ አሠራሩ ምን ይመስላል?

- ❖ የቅሬታ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡

19. በማንኛውም ምክንያት አጉል ተስፋ በመስጠት ዜጋውን የማይፈጸምለት ጉዳይ እንዳይመላለስና እንዳይጉላላ የተደረጉ መሻሻሎችና ጥረቶች የተገኙ ውጤቶች በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? አመራሩ አጉል ተስፋ መስጠትን መሆኑን ተገንዝቦ እየሰራ ነው ወይ? አብነት ይጠቀስ

- ❖ አጉል ተስፋ የመስጠት አሠራር የለም፤ሊፋጸም የማይገበውን እንደማይሆን እና የማይሆንበትን ምክንያት በመግለጽ አምኖ እንዲሄድ አመራሩ አምኖ እየሠራበት ነው፡፡

20. የህዝብ ፍላጎትና ቅሬታ የሚታወቀበት የሠራር ሥርዓት ከመዘርጋት አንጻር የተደረጉ ጥረቶች ማለትም ቅኝት/Survey/ማድረግ የመሳሰሉ ሥራዎች በምን ደረጃ ይገኛሉ?

- ❖ ህዝቡ ፍላጎቱን የሚገልጽበት የቅሬታ የአሠራር ስርዓት ተዘርግቷል፡-ይኸውም የቅሬታ ቅጻቅጾችን በየደረጃ በመዘርጋት፣የአስተያየት መስጫ ሰጥን በመዘርጋት እና የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በየደረጃ በማቋቋም እየተሰራበት ነው፡፡

## የግልጸኝነትና ተጠያቂነት አሠራር

21. በውሳኔ አሰጣጥ የዕቅድ አፈጻጸም እንዲሁም ህግ፣መመሪያና አሠራርን በተመለከተ ለህዝብ የማሳወቅና ግልጽ የማድረግ አሠራር ደብሯል ወይ?

- ❖ በውሳኔ አሰጣጥ የዕቅድ አፈጻጸም፤ህግ ፣መመሪያ እና አሠራሮችን በተመለከተ ለህዝቡ የማሳወቅ እና ግልጽ የማድረግ አሠራር ተዘርግቷል፡፡ ይኸውም መመሪያ፣ደንብ እና አሠራሮች በተመለከተ ግልጽ ለማድረግ በአብዛኛው ዞን እና ወረዳ ሴክተሮች ዝርዝራቸውን በማስቀመጥ እየተሠራበት መሆኑን እና በቀበሌያት ደረጃ አነስተኛ ወንጀሎች ስፈጸሙ በተፈጸመበት ውሳኔ በማስተላለፍ በቦታ ላይ እንዲለጠፍ በማድረግ ህብረተሰቡ እንዲማርበት እየተደረገ ነው፡፡

22. ህዝቡ በመደበኛ ፕሮግራም የዕቅድ አፈጻጸምን እንዲገመግም ይደረጋል ወይ?

- ❖ በተቀናጀ አሠራር ህዝቡ የዕቅድ አፈጻጸም ይገመግማል፡፡

23. ከዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ እስከ አፈጻጸሙ ተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚሳተፍበትና እንዲያውቀው የሚደረግበት አሠራር ምን ይመስላል?

CAPACITY

- ❖ ህዝቡ ከማቀድ ጀምሮ ተሳታፊ በመሆን የተፈጸመውንና ያልተፈጸመውን በመገምገም ጥሩ አፈጻጸም ላሳየው የሚመሰግንበት እና የሚበረታታበት ሥርዓት እንዳለ እና በተዋረድ የሚኮነንበት እና የሚጠየቅበት ሥርዓት አለ፡፡

24. ለግልጸኝንትና ለተጠያቂነት አመቺ የሆኑ አሠራሮችን ለመዘርጋት የተደረገው ጥረት ምን ይመስላል?

- ❖ ለግልጸኝነት እና ለተጠያቅነት አመቺ የሆኑ አሠራሮች ለመዘርጋት ጥረት ተደርጓል፡፡ መመሪያ እና አሠራሮችን ግልጽ ለማድረግ ዝርዝሮች በግልጽ ለህብረተሰቡ ይለጠፋል፡፡ ውሳኔዎች ህብረተሰቡ እንዲማርበት ግልጽ የሆነ ቦታ ይለጠፋል/ማሌ፣ሰሜን አሪ፣ደቡብ አሪ፣በበና ፀማይ ወረዳዎች/

25. ቅሬታ ያለው ቅሬታውን የሚያስማበትና መልስ የሚያገኝበት አሠራር ተዘርግተዋል ወይ? ለምሳሌ ቅሬታውን የሚያደምጥበት አካል

- ❖ ቅሬታ ያለው ቅሬታውን የሚያሰማበት ሥርዓት እና አሠራር በሁሉም ወረዳ እና በአብዛኛው ቀበሌያት ተዘርግቷል፡፡

26. ባለጉዳይ በሚሰጠው አገልግሎት ቅሬታ ካለውና በተሰጠው አገልግሎት እርካታ ካላገኘ የአስተያየት መስጫና ቅሬታውን የሚገልጽበት አሠራር ተፈጥሮሃል ወይ?

- ❖ ባለጉዳይ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ ቅሬታ ካለውና በተሰጠው አገልግሎት ካልረካ በፅሑፍ አስተያየት መስጫ ቅጻቅጾች እንዲሁም በቃል አስተያየት የሚሰጥበት አሠራር ተፈጥሯል፡፡በተጨማሪም የአስተያየት መስጫ ሳጥን እና ሌሎች ምልክቶች ተዘርግቷል፡፡

27. የወረዳና ቀበሌ ደረጃ ጉዳይ ተቀባይና የመረጃ ዴስክ ተቋቁሞ ባለጉዳይ በቀላሉ አገልግሎት የሚያገኝበት ሥርዓት ለመፍጠር የተደረገው ጥረትና የተገኙ ውጤት ምን ይመስላል?

## ፍትሃዊነትና የህግ የበላይነት

28. ህብረተሰቡ በፍትሃዊነትና ህግ የበላይነት ተጠቃሚ ለማድረግ ከህገ-ወጥ ድርግቶች፣ከሙስናና አድሎ፣በደል ከማድረስ እንዲሁም ለሚገባውቸ የሚገባውን እንዲገኝ አለማድረግ ከመሳሰሉ ነገሮች የጸዳ አሠራር ለመከተል ያለው ጥረትና የተገኙ ውጤቶች ምን ይመስላሉ?

- ❖ ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው፡፡በዚህ ረገድ በዘር፣በብሔር፣በፆታ ፣በቋንቋ እና በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ መንግስት በዘረጋ በማንኛውም ነገር ከህገ-ወጥ፣ ከሙስና ና አድሎ አሠራር የጸዳ አሠራር በማካሄድ በተሻለ መጠን ለሚገባቸው የሚገባቸውን እንዲያገኙ ያለው ፍትሃዊነት ከነባሩ አሠራር የተሻለ ከመሆኑም ባሻገር የተገኙ ውጤቶች አበረታች ናቸው፡፡በተለይ አላግባብ ዘጋን ማሰርና ፣ማስፈራራት እና መደብደብ ቀንሷል፡፡ያለደረሰኝ ንብረት/ገንዘብ/ መያዝና መውሰድ እንዳይኖር ተደርጓል፣ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የዜጋ ቤት መበርበር እንደነውር ተቆጥሮአል ፡፡

## ቀልጣፋነትና ውጤታማነት

29. የሥራ ቅልጣፌና ውጤታማነትን ለማምጣት የተዘረጉ የአሠራር ሥርዓቶች ማለትም /ከዕቅድ ዝግጅት ከሪፖርት አዘገጃጀት አቀራረብ/ በምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ ምን ውጤት አስገኝተዋል?

CAPACITY

❖ የዚህ መርህ ዋነኛ ይዘት የማቀድ፣የመፈጸም ሆነ የማስፈጸም ፍጥነት የሚፈለገውን እና የሚገባውን ውጤት ማምጣት መቻል ስለሆነ በበላይ ሥራ አመራር በተዘረጋ አሠራር ስትራቴጅክ ዕቅድ እና ዓመታዊ ዕቅድ ተዘርግቶ በየደረጃ በማስተባበር መልካም ተሞክሮ የታየበት ነው፡፡ሆኖም ግን የመረጃ /የሪፖርት/ልውውጥ አሠራር ደካማ ነው፡፡የቀልጣፋ እና የውጤታማ አሠራር ችግሮች/እንቅፋቶች/ ለምሳሌ አደረጃጀቶች እና አሠራሮች በመሠረታዊ ሥራ ሂደት ስለተለወጠ ከኃላፊ እስከ ፈጻሚ ውሳኔ በማስተላለፍ ተገልጋይ የማርካት ሥራ እና አበረታች ውጤቶች ታይቷል፡፡

30. <u>ከአደረጃጀት አንጻር</u>

- በምን ያህል ቀበሌና ወረዳ የቀበሌ አደረጃጀት በቀበሌ አሠራርና በመንደር ተወካዮች ጋር በመሆን ህዝቡን በቀጥታ በማግኘት የልማት ዕቅደቸውን እየፈጸሙ ነው? ብዛታቸው ይገለጽ?
  - ❖ በመቶ አርባ ስምንት/148/ቀበሌያት ላይ የቀበሌ አደረጃጀት/ የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ/ አሠራር ተዘርግቷል፡፡እንዲሁም በአብዛኛው መንደሮች የመንደር ተወካዮች ተዘርግቶ የልማት ዕቅዶችን እየፈጸሙና እያስፈጸሙ ነው፡፡
- በምን ያህል ቀበሌ ወረዳ አራቱ የልማት ኮሚቴዎች በሚገባ ተደራጅተው በቅንጅት እየተሰራ ይገኛል?

<u>አራቱ የልማት ኮሚቴዎች በአብዛኛው ተደራጅተው በቅንጅት የሚሰሩበት ወረዳ እና ቀበሌያት ስም ዝርዝር</u>

| ተ.ቁ | የወረዳው ስም | አራቱ ኮሚቴዎች በአብዛኛው የሚታዩበት ቀበሌያት ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ጂንካ ከተማ አስ/ር | 1 |
| 2 | ማሌ ወረዳ | 11 |
| 3 | ሐመር ወረዳ | 15 |
| 4 | ኛንጋቶም ወረዳ | 5 |
| 5 | ደቡብ አሪ ወረዳ | 5 |
| 6 | ሰሜን አሪ ወረዳ | 4 |
| 7 | በና ፀማይ ወረዳ | 5 |

- በቀበሌያችሁ ደረጃ ምን ያህል መንግስታዊ መዋቀረት ያልሆኑ በፍቃደኝነት የተደራጁ የልማት ቡድኖች ይገኛሉ አፈጻጸማቸው በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?

CAPACITY

- መንግስታዊ ያልሆኑ የተደራጁ የልማት ቡድኖች ቢኖሩም በቁጥር አይታወቅም፡፡

**የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ እንቅስቃሴን በተመለከተ**

31. የቀበሌው ሥራ አስኪያጅ ከህዝብ ተመራጮች ወይም ከቀበሌ ካቢኔ አካላት ጋር ያለው ግንኙነትና የሥራ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?
    - የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ ከህዝብ ተመራጮች ወይም ካቢኔ አባላት ጋር ያላቸው የሥራ እንቅስቃሴን በተመለከተ የካቢኔ አባላት በቋሚነት የሚሰሩት ሌላ ሥራ ስላላቸውና ሌሎቹም በቀበሌ ደረጃ ያሉ ሙያተኞች በቋሚነት ሌላ ሥራ ስለምሰሩ የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች የካቢኔ ውሳኔዎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ከማድረግ በተጨማሪ በየእለቱ መሰራት ያለባቸውን የቀበሌውን ሥራ በማስተባበር ለምሳሌ ባለጉዳይ ማነጋገር፣መረጃ መስጠት ፣ መልዕክት መቀበል እና የቀበሌውን መረጃ በማጠናከር እለት ተእለት በመሥራት በተቀናጀ አሠራር ሥራውን በጋራ የሚተገበርበት ይሆናል፡፡
32. ከትምህርት፣ከጤናና ከግብርና ባለሙያዎች ጋር በማቀናጀት የቀበሌውን ዕቅድ ከመምራትና ከማስፈጸም አንጻር የሥራ አስኪያጅ ሚና ምን ይመስላል?
    - ከአገራዊ ራዕይ በተዋረድ በቀበሌ ደረጃ በሚገባ አሳብን ተንሸራሽሮ የጋራ መግባባት በመፍጠር በተሻለ መጠን ዕቅዶች እንዲወራረሱና እንዲቀናጁ ከትምህርት፣ከጤናና ከግብርና ባለሙያና ከቀበሌ ሥራ አስኪያጅ ጋር በማቀናጀት የቀበሌውን ዕቅድ ያዘጋጃሉ፡፡ ለማስፈጸምም ያስተባብራሉ፣ለሚመለከተው አካልም ሪፖርት በሥራ አስኪያጅ በኩል ይቀርባል፡፡
33. በሁሉም የገጠር ቀበሌ የቀበሌውን ሥራ አስኪያጁ አሰልጥኖ ሥራ ለማስጀመር እንዲያስችል አስፈጊው ግበዓት ከሚሟላት አንጻር የተደረገው ጥረትና የተገኙ ውጤቶች ምን ይመስላል?ለምሳሌ የሥራ አስኪያጁ ምደባ፣ጽ/ቤትና የቢሮ መገልገያ ቁሳቁስ
    - በገጠር ቀበሌያት ደረጃ ሥራ አስኪያጅ አሰልጥኖ ሥራ ለማስጀመር እንዲያስችል በየደረጃ የአሰልጣኝ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በአብዛኛው ቀበሌያት ሥራ አስኪያጅ ተመድቦ፣የጽ/ቤት መገልግያ ቁሳቁሶች በማሟላት ሥራው እየተሰራ ነው፡፡በዚህም ምክንያት የተገነ ውጤት ቀበሌያት በዕቅድ መመራታው፣ጉዳይ ተቀባይ በማቋቋሚ ቅሬታ እንዳይሰራራ ማድረግ፣ፋጣን መረጃ ማግኘት መቻልና ወ.ዘ.ተ

## ሐ.የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም በተመለከተ

.የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ (በዞንና ወረዳ)

1.የዞኑ ፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ በየሴክተሩ የሚካሄደውን የፍትህ ሥርዓት እንቅስቃሴ በባላይነት እየመራ ጉድላቶችንና ክፍተቶችን በማስተካከልና ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት የሚቀርቡበት የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ሥርዓቱን ተቋማዊ እንዲደረግ ተደርጓል፡፡

2.የፍስማፕ የ2001 ዓ.ም ዕቅድ ለማዘጋጀት ክፈተቶችን በመለየት ወደ ሥራ ገብቷል፡፡በሰሜን አሪ፣ በበና ፀማይ፣በደቡብ አሪና በዳሰነች ወረዳዎች ፍስማፕ ለማሻሻል እና ለማስተባበር በሚያስችል

CAPACITY

ሁኔታ ዕቅድ ተዘጋጅቶ አስተባባሪና ቴክኒክ ኮሚቴ የተመቻቸ አሠራር እንዲኖር በማድረግ እየተሰራበት ነው፡፡

3.ሁሉም/ፍ/ቤት፣ዓቃቤ ህግ፣ፖሊስና ማረሚያ /የጋራና የተናጠል ተቋማዊ ለውጡን አሟልተው እንዲተገበሩና የተናጠልና የጣምራ ሥራ እንዲያጠናክሩ በተደረገው አሠራር ለህብረተሰቡ ያስገኘው አዲስ ለውጥ መኖሩ በተለይ ወንጀል ቀንሷል፡፡ያለፍርድቤት ትዕዛዝ ዜጋን ማሰር ቀንሷል፡፡

## የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም በተመለከተ

1. በፍርድ ቤቶች የፍርድ ሂደት ቀልጣፋ ለማድረግ የተሰራ ሥራና የተዘረጋ ሥርዓት በአጭሩ ቢገለጽ
    - በአንድ ቀን/ጊዜ/ ማስረጃና መከላከያ ወይም የተከሳሽና ከሳሽ ማስረጃ መስማት
    - በተለያዩ ወረዳ እና ቀበሌያት የተዘዋዋሪ ችሎት መሥራት
    - ክሶችን በተለያየ አቀራረብ ማለትም በተፈጠነ፣በአጭር እና መደበኛ በማለትና በመለያየት እንደጉዳዩ ዓይነት በመወሰን
    - የተለያዩ የትዕዛዝ ውሳኔ ፎርማቶች እንዲሁም ፎቶ ኮፒ ማሽኖችን መጠቀም
2. የማህበራዊ ፍ/ቤቶች በተሰጣቸው ሥልጣን ለህብረተሰቡ በመስጠት ያሉት አስተዋጽኦ በዝርዝር ቢገለጽ
    - ባለጉዳዮች በጥንቃቅንና በአነስተኛ ጉዳዮች ጊዜያቸውን በማጥፋት እስከ ወረዳ በመንዝ የሚደርስባቸውን እንግሊት በመቀነስ በየቀበሌው በስልጠናቸው ልክ ፍትህ በየአቅራቢያቸው እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡
3. የማህበራዊ ፍ/ቤቶች ተግባራዊ የልሆኑበቸው ቀበሌዎችና ምክንያቱን እንዲሁም ያጋተማቸውን ችግር በዝርዝር ቢገለጽ
    - የማህበራዊ ፍ/ቤት ተግባራዊ ያልሆነበት ቀበሌ የለም ሆኖም ስልጠና የተሰጣቸው ዳኞችና ሬጂስትራሮችን የቀበሌ አስተዳደሮች በማንሳት ስልጠና ያልወሰዱትን የማቀመት ሁኔታ በክፍል ይታያል፡፡
4. በዞኑና በወረዳዎች የተዘዋዋሪ ችሎት በሚካሄድባቸው ቦታዎች ብዛታቸውን በዞንና በወረዳ ቢገለጽ
    - በዞኑ ከፍ/ቤት፡-ደቡብ አሪ ወረዳ ቶልታ ቀበሌ ላይ

      -ማሌ ወረዳ ሌሞ ጌንቶ » »

      -በና ፀማይ ወረዳ ቀይ አፈር » »

      -ሐመር ወረዳ ዲመካ » »

      -ሳላማጎ ወረዳ ሐና » »
    - እንዲሁም በወረዳ ፍ/ቤቶች

      ደቡብ አሪ ወረዳ ፍ/ቤት -ቶልታ ቀበሌ ላይ

      -ጂንካ ከተማ ላይ

      ማሌ ወረዳ ፍ/ቤት - ባላ ቀበሌ ላይ

CAPACITY

በና ፀማይ ወረዳ ፍ/ቤት -ቃቆ ቀበሌ ላይ

- ብራይሌ ቀበሌ ላይ

ሐመር ወረዳ ፍ/ቤት -ቱርሚ ቀበሌ ላይ

ሳላማጎ ወረዳ ፍ/ቤት -ጊዮ ቀበሌ ላይ ተዘዋዋሪ ችሎቶች ይካሄዳሉ፡፡

5. የተዘዋዋሪ ችሎት በሚካሄድባቸው ቦታዎች ያጋጠማቸው ችግር ካለ በዝርዝር ቢገለጽ

- የችሎት አደራሽ አለመኖር
- የሠራተኞች ማደሪያና ምግብ አለመቻቸት
- ተፈላጊ ባለጉዳዮች ማለትም ማስረጃና ተከሳሽ አልፎ አልፎ አለመቅረብ
- የተሽከርካሪ አለመኖር
- የበጀት ዕጥረት

<u>የተወሰደ እርምጃ</u>

- የችሎት አደራሽ ችግርን ለመቅረፍ በቀበሌ ጽ/ቤትና ፖሊስ ጣቢያዎችን መጠቀም
- የማደሪያ ችግር ለመቅረፍ በአቅራቢያ ከሚገኙ ስዎች /ነዋሪዎች/ጋር በመደበልና ክፍት የቀበሌ ቤቶችን መጠቀም
- ምግብ በራስ ሰርቶ መጠቀም
- ተፈላጊዎች ሳይቀርቡ ስቀሩ በመሃል እንዲቀርቡ በማዘዝ መስማት
- የተሽከርካሪ ችግርን ለመቅረፍ በየጊዜው ያላቸውን ያረጀውን አሮጌ መኪና ማስጠገንና አልፎ አልፎ ሌሎች መ/ቤቶች ትብብር መጠየቅ እንዲሁም በሞተር ሳይክሎች መገልግልና የሕዝብ ትራንስፖርት መጠቀም
- የበጀት ችግርን ለመቅረፍ የተሰጠውን አብቃቅቶ መጠቀምና በመሐል ጉድለት ሲያጋጥም ከአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ ጋር በመነጋገር ተጨማሪ በጀት ማስፈቀድ

6-7 በዞኑ የቪዲዮ ችሎት የሚካሄድባቸውን ቦታዎችና ብዛታቸውን በወረዳ በመለየት በዝርዝር ቢገለጽ በቪድዮ ችሎት አሰጣጥ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም የታየ ችግርና ወደፊት

መወሰድ የሚገባ የመፍትሄ እርምጃ ተለይቶ ቢቀመጥ

- በቪዲዮ ኮንፍረንስ የሚሰራበት ችሎት በዞናችን ሆኖም በመቅረጸ ድምጽ አጠቃቀምና አቀራረጽ እንዲሁም የዳታ ቤዝ አጠቃቀም ላይ በቂ ዕውቅት ያለው ባለሙያ ባለመኖሩ መጠቀም አልተቻለም፡፡

8. ከመደበኛ ችሎት፣ተዘዋዋሪ ችሎት እና ቪዲዮ ችሎት ወጪ መደበኛ ክርክር በተገልጋዩ አቅራቢያ በማድረግ በዘላቂነት የተዘረጋ ሥርዓት ካለ ቢገለጽ

   - የለም

9. በይግባኝ ክርክር ይግባኝ ገልብጦ በመስጠት በተገልጋዩ ላይ ያስገኘው ለውጥ

- በይግባኝ ክርክር ይግባኙን ገልብጦ በመስጠት በተገልጋዩ ያስገኘው ለውጥ በፎቶ ኮፒ በመጠቀም ቀደም ሲል በእጅ ስገለበጥ ይፈጅ የነበረውን ጊዜ እና የባለጉዳይ እንግሊት አስቀርቷል፡፡

10. በፍርድ ቤቶች በዳኝነት ሥራ ሥልጣናቸው በሚወስኑ ጉዳዮች የፍርድ ጥራትን ለመለካት በተቀመጠ STANDARD መሠረት እየሠሩ ናቸው ወይ ከልተደረገ የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ ወይም ማስተካኪያ በዝርዝር ቢቀመጥ
    - ጥራትን ለመለካት የወጣ መለኪያ አልነበረም
11. ምርጥ ተሞክሮን ወይም አስተማሪ የሆኑ የፍርድ ውሳኔዎች በማስተማሪያነት ለሌሎች ለማስተዋወቅ እንዲቻል ምርጥ ተሞክርና አስተማሪ የሆኑ ውሳኔዎች በዝርዝር ቢቀመጥ
    - ደቡብ አሪ ወረዳ ፍ/ቤት የመድፈር ሥራ በፈጸመ ግለሰብ ላይ 48 ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ /41/ሰዓት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት መቻሉ፡፡
    - የስርቆት ወንጀል ስፈጽም የተያዘ በ6 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት
    - ደቡብ ኦሞ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጋዘር ከተማ ውስጥ ባሏን በግፍ የገደለችውን ግለሰብ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ በዕድሜ ልክ ፅኑ ዕስራት መቅጣት መቻሉ፣
    - በጋዘር ከተማ ውስጥ ሚስቱን በግፍ የገደለውን ግለሰብ በተያዘ በ25 ቀን ውስጥ የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ፍርድ መወሰን መቻሉ፣
  - የዳሰነች ብሔር ተወላጆችን የገደሉ ሐመሮች ላይ በ18 ቀን ጊዜ ውስጥ ፈጣን ፍርድ መወሰኑ፣
12. የኢኮኖሚ አቅማቸው ዝቅተኛ ለሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች በወንጀል ተካሰው ለህግ ሲቀርቡ በመንግስት ወጪ ጠበቃ እንዲቆምላቸው በተዘረጋ ሥርዓት የተጠቃሚዎች ብዛት
    - የለም
13. የጉዳዮች ክምችት ለመቀነስ በተደረገ ጥረት ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች ብዛት በቁጥር
    - ውሳኔ ያገኙ መዝገቦች ብዛት 6667/ስድስት ሺ ስድስት መቶ ስልሳ ሰባት/
14. ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች ብዛት በቁጥርና በመጠን ከነምክንያታቸው
    - ውሳኔ ያላገኙ/ለሚቀጥለው የተላለፉ/መዝገቦች ብዛት 1871/አንድ ሺ ስምንት መቶ ሰባ አንድ/ ምክያቱም -የማስረጃና ተከሳሽ አለመቅረብ

      -የባለሙያ ዕጥረት

      -የበጀት ዓመቱ ካለቀ በኋላ አዳዲስ መዝገቦች መቅረብ
15. የጥብቅና ፈቃድ ያላቸው ባለሙያዎች በነጻ ጥብቅና የሰጧቸው ባለጉዳዮች ብዛት
    - የለም
16. የስነ- ምግባር ማካታተያ ሥልጠና ለደኞችና ዓቃቢያን ህግ በተዘጋጀው ሰነድ ላይ ለሁሉም እኩል የሚዳኝ ሥርዓት ተዘረግቷል በዚህ መሠረት ከስልጠና በኋላ በስነ ምግባራቸው ተለይተው የወጡ ዳኞችና ዓቃቢያን ህግ ብዛታቸው ቢገለጽ በሥነ ምግበር ጉድለት ተለይተው እርምጃ የተወሰደባቸው ዳኞችና ዓቃቢያና ህግ ብዛታቸው ቢቀመጥ

CAPACITY

- የለም

17. መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ከሙከራ ትግበራ ወደ ሙሉ ትግበራ ለመግባት የተደረገ ቅድሚያ ዝግጅት በአጭሩ ቢቀመጥ

  - በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ከሙከራ ትግበራ ወደ ሙሉ ትግበራ ለመግባት የተደረገ ዝግጅት -የሠራተኛ ምልመላ ማጠናቀቅ

    - በምልመላ ለተካተቱ/ምደባ ላገኙ/ የዞንና የሁሉም ወረዳ ፈጻሚዎች ስልጠና መስጠት

    -ስለአተገባበሩ በተግባር ማሳየት

## የዓቃቤ ሕግ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

1. በወንጀል የተጠረጠሩ ግለሰቦች ምርመራ በፖሊስና በዓቃቤ ህግ በጋራ እንዲካሄድ በተዘረጋ ሥርዓት የተከናወኑ ተግባራት በአሠራር ያጋጠሙ ችግር
   - ✓ የባለሙያዎች ድልድል እና ሥልጠና ተሰጥቷል የሙሉ ትግበራው ከሐምሌ 1/2001 ጀምሮ በለመጀመር የተከናወኑ ተግባራት የሉም ሆኖም ለሙሉ ትግበራው አመች የሆኑ የሥራ ቦታ/ሰፋፊ ቢሮ/ በማዘጋጀት ላይ መሆናቸው
2. የምርመራ መዝገብ ተጠናቆ ከደረሰ በኂላ ክስ በጋራ በፖሊስና ህግ የሚቀረብበትና ውሳኔ በዳኛ የሚሰጥበት ሥርዓት በቀናት ርዝማኔ ላይ ያስገኘው ለውጥ
   - ✓ ገና ሙሉ ትግበራውን ስላልጀመሩ መግለጽ አስቸጋር ቢሆንም በሰነዱ መሠረት የተወሰነው ጊዜ 2 ወር ብቻ ነው፡፡
3. የማስረጃ አቀራረብና ቀጠሮ መራዘም ለማስቀረት በተዘረጋ የአሠራር ስርዓት የተገኘ ለውጥ በሂደቱ ያጋጠማቸው ችግር
   - ✓ ለማስረጃ አበል በጀት ተይዞ ለምስክሮች የወጭ ማካካሻ አበል ባለመከፈሉ የማስረጃ አቀራረብ በጣም ደካማ መሆኑ
4. በዳኛው በዓቃቤ ሕግና ፖሊስ ውሳኔ አሰጣጥና ክስ አቀራረብ ግድፈት የፍርድ ሂደት መጓጸጽ በመከተሉ በባለሙያዎች ላይ የተወሰደባቸው ርምጃና ብዛታቸው ተለይተው ቢገለጽ
   - ✓ የለም
5. የውልና ማስረጃ ፣የማህበራት ምዝገባ ጥብቅና ፈቃድ ለመስጠት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በግልጽና በዝርዝር ስለመለጠፋቸው
   - ✓ ተለጥፎአል
6. ፋይሎችንና የማህደራት አያያዝን ዘመናዊ ለማድረግ በተዘረጋ የአሠራር ሥርዓት የተገኙ ውጤት በዝርዝር ቢቀመጥ----------ዘመናዊ የተደረጉ በየደረጃ ያሉ ፍርድ ቤቶች ማለትም የመጀመሪ ደረጃ ፍ/ቤት -----ከፍተኛ ፍ/ቤት -------እና ጠቅላይ ፍ/ቤት ------

CAPACITY

ሙሉ ለሙሉ ዘመናዊ የተደረጉ ----በከፊል ዘመናዊ የተደረጉ------ዘመናዊ ያልተደረጉ በሁሉም ፍ/ቤቶች ደረጃ በዝርዝር ቢገለጽ ከምክንያት ጭምር---

- ✓ ለዓቃቤ ሕግ የተደረገ የዘመናዊ አሠራር/ኮምፒውተራይዘሺን/ ሥልጠናም ሆኖ የኮምፒውተር ድጋፍ የለም ሥራውም በቀድሞው አሠራር እየተሠራ ነው፡፡

7. የሕግ ንቃት ትምህርት የተሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍል ብዛት ወንድ----ሴት----- ድምር----
8. በወንጀል ሰለባ ለሆኑና ጥቆማ አቅራቢዎች /ምስክሮች/የደህንነት ጥብቃ ስለመደረጉና ተደርጎ ከሆነ የተጠቀሙበት ሥልትና ጥብቃ ያገኙ ብዛት
   - ✓ የተጠናከረና ውጤታማ የሆነ የጥበቃ /ደህንነት/ሥራ አልተሠራም አደረጃጀቱም ገና ነው፡፡
9. በወንጀል ክስ ማስረጃ አቅራቢዎች ወይንም ምስክሮች በራስ ወጪ መጓጓዣን ለመተካትና በመንግስት ለመሸፈን የተሰራ ሥራ /የተመደበ ሥራ ላይ የዋለ ገንዘብ መጠን/---
   - ✓ የለም
10. የንጹሐንን መብት የሚያስፈገፍሩ በሐሰት መስካሪ ግለሰቦች በሕግ ተጠያቂ የሚያደርግ አሠራር ሥርዓት ተግባራዊ በተደረገበት ሁኔታ በህግ ተጠያቂ የሚያደርግ አሠራር ተጠያቂ ያልሆነበት ሁኔታ ካለ በአጭር ቢገለጽ
    - ✓ ተጠያቂ የሆኑና የተቀመጡ ጭምር አለ፡፡
11. ፍትህን በፍጥነት አቀላጥፎ ለመስጠት የሚቻልበትን አደረጃጀት መሠረት ያደረገ የሰው ኃይል ስለመሟላት
    - ✓ በቂ የሰው ኃይል /የባለሙያ ኃይል/ የለም፡፡ ምክንያቱም የበጀት እጥረት አለ እየተባለ እና ለፍትህ ሴክተሩ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ በቂ በጀት ባለመመደቡ ነው፡፡
    - ✓ ከባለሙያው ብዛትና ብቃት ማነስ ጋር የሥራ ማስከጃ በጀት እና ቀሳቁስ እጥረት ሌሎች የፍትህ ሴክተሩ ችግሮች ናቸው፡፡
12. አሳሰራ ያሉትን ህጎች ለማሻሻል የተደረገ ጥናትና ጥራት እንዲሁም የተወሰደ መፍትሄ---
    - ✓ አንዳንድ ህጎች በመንግስት ደረጃ እየተሻሻሉ ነው በውይይት እያዳበር ነው፡፡
13. ከBPR አተገባበር አንጻር ውጤት ያጋጠማቸው ችግር እንዲሁም ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች ተለይተው ቢቀመጥ---
    - ✓ የBPR ጥሩ ነው፡፡በተለይ በፍትህ ሴክተሩ ላይ ትልቅ ለውጥ ያመጣል ሆኖም ግን የህግ ማዕቀፍ የሚያስፈልጋቸው ትላልቅ ችግሮች ስላሉ ለእነርሱ ጉዳዮች በፍጥነት ህግ ሊወጣላቸው ይገባል፡፡እንዲሁም ለሴክተሩ ትኩረት ተሰጥቶት በቂ በጀት ቁሳቁስና ባለሙያ ማሟልት ይገባል፡፡

CAPACITY

## ፖሊስ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

1. የሕብረተሰቡን ሰላምና ደህነት ለማስጠበቅ ፖሊስን የማስፈጸም አቅም ለማሳደግ የተሰጠ የሥልጠና ዓይነትና የሰልጣኝ ብዛት ፣በዞንና በወረዳ ወ-- ሴ---
   - ➢ ህብረተሰቡን በኮሚዩኒቲ ፖሊስንግ ትግበራ ውስጥ ባለቤት ማድረግ እንዲቻል የኮሚዩኒቲ ፖሊስንግ ጽንሰ ሐሳብና ሲትራቴጂ ላይ አባለት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
   - ➢የኮሚዩኒቲ ፖሊስንግ የአተገባበርና አፈጻጸም ስልት ማኑዋል ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
   - ➢በBPR ስትራቴጂና አስፈላጊነት ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
   - ➢አዲሱ የወንጀል መከላከል ማስፈጸሚያ ማኑዋል ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
   - ➢የ2002 በጀት ዓመት ዕቅድ አዘገጃጀት ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ወንድ 548 ሴት 44 ድምር 592 ለፖሊስ አባለት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
   - ➢በ2001 ዓ.ም በተዘረጋ አሠራር በፖሊስ ማሻሻያ ፕሮግራም የኮሚዩኒቲ ፖሊስንግ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ወንድ 147863 ሴት 76803 ድምር 224666 የተለያየ ህብረተሰብ ክፍል ስልጠና ወስዷል፡፡
2. ሕብረተሰቡን በወንጀል መከላከል እንዲሳተፍ ለማድረግ የተደረጉ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት በዞን፣በወረዳና በቀበሌ ------------ተከታታይነት ያለው የወንጀል መከላከል ሥልጠና ለህብረተሰቡ እንዲሰጥ የተወጠና ዕቅድና ስልት በዝርዝር ቢቀምጥ
   - ➢ ህብረተሰቡን በወንጀል መከላከል እንዲሳተፍ ለማድረግ በአዲሱ ሥራ ሂደት የፖሊስ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ በሁሉም ቀበሌያት ውስጥ የኮሚዩኒቲ ፖሊስንግ አማካሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ እስከ ጎጥ ድረስ ህዝቡ ትምህርት በቀላሉ በሴል አደረጃጀት ማስተማር የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡
3. ኮሚዩኒቲ ፖሊስንግን በማጠናከርና በወንጀል መከላከሉ ሂደት የተመሠረተባቸው ወረዳና ቀበሌ ተለይቶ ቢገለጽ--------ኮሚዩኒቲ ፖሊስንግ ለአካባቢ ህብረተሰብ ወንጀልን በመከላከል የሰጠው አስተዋፅዖና ካለፈው ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር በአሁኑ ወቅት ወንጀል በምን ያህል ቀንሷል በዝርዝር ቢቀመጥ
   - ➢ የኮሚዩኒቲ ፖሊስንግ ለዞኑ በሁሉም ወረዳዎችና ቀበሌያት የተዘረጋ ሲሆን ከአምናው የዘንድሮ በ75% ወንጀል ቀንሷል፡፡
4. የኮሚዩኒቲ ፖሊስንግ አተገባበር ከራስ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጋናዝቦ ለመሄድ የተደረገ ጥረት በወረዳ ተለይቶ ቢገለጽ
   - ➢ የኮሚዩኒቲ ፖሊስንግ በወረዳዎች ውስጥ በተዘረጋባቸው ቀበሌያት የሚተገበር ቢሆን አፈጻጸሙም የቀበሌ የወንጀል ችግር መነሻ በማድረግ በቀበሌ ህዝብ እንዲሁም በአመራርና በፖሊስ አባላት በጋራ የአፈታት ስልት ዕቅድ በማዘጋጀት ይተገበራል፡፡

CAPACITY

5. የኮሚዩኒቲ ፖሊስንግ አደረጃጀት ያልደረሰባቸውን ወረዳና ቀበሌ ተለይቶ ቢገለጽ---በአደረጃጀት ያጋጠማቸውን ችግር በዝርዝር ቢቀመጥ
   - የኮሚዩኒቲ ፖሊስንግ አደረጃጀት ያልተደረገባቸው ወረዳዎችና ቀበሌያት የሌሉ ሲሆን በአርብቶ አደር ወረዳዎች ህ/ቡ ከቦታ ቦታ የሚዘዋወር በመሆኑ የነበረበት ቀበሌ ለቆ የመሄድና ያለመገኘት ችግሮች የሚፈጠሩ ሲሆን በቀበሌ የተዋቀሩ የፀጥታ ኮሚቴዎች በዚያ መልኩ ለተወሰነ ጊዜ የማይገኙ በመሆኑ የሥራዎች መቆራረጥ ይፈጠራል፡፡
6. ከኮሚዩኒቲ ፖሊስንግ አደረጃጀት ውጪ የአከባቢው የፀጥታ ችግሮች ለማስወገድ ሌላ የተዘረጋ የአሠራር ሥርዓት በአጭሩ ቢገለጽ
   - የለም
7. የወንጀል ምርመራ ሥራን ለማቀላጠፍ ከተሰራ ሥራ በሰዓት ቀናት ምርመራ ተጠናቆ ለዳኛው ይቅረብ ነበረ? አሁንስ--
   - ምርመራ ሥራ በፍጥነት አጣርቶ ለማቅረብ የወንጀሉ ዓይነትና የማስረጃዎች በቅርበት መገኘት የሚወስን ሲሆን በአሁኑ ጊዜ እጅ ከፍንጅ ወንጀሎችን ወዲያውኑ ከግማሽ ቀን እስከ አንድ ቀን ተጣርተው ይጠናቀቃሉ፡፡
8. ተጠርጣሪ ወንጀለኛ ከመያዙ በፊት መረጃ የሚሰበሰብ ሥራ ቅድሚያ ተሰጥቶበት የተሰራ ከሆነ የተሰራ ሥራ በፐርሰንት ቢቀመጥ----ከልተሰራ ለምን ከነምክንያቱ---
   - ማንኛውም ተጠርጣሪ እጅ ከፍንጅ ወንጀል ሲሰራ ከልተገኘ በስተቀር አይያዝም ወንጀል ፈጽመሃል ተብለው ለሚቀርቡ ክሶችም በቅድሚያ የማስረጃ ማሰባሰቡ ሥራ ሳይጠናቀቅ የሚያዝ ተጠርጣሪ የለም፡፡
9. ተጠርጥረው የታሠሩ ወንጀለኞች ምን ያህሉ የጊዜ ቀጠሮ ተጠይቆባቸዋል በቁጥር ቢቀመጥ-----
   - የተፈጸሙት ወንጀል በስፋትና በጥልቀት ማጣራት ያለባቸው ጉዳዮችና በፖሊስ የዋስትና መብታቸው መጠበቅ ለማይቻልባቸው ክሶች በቁጥር መጠኑን መግለጽ ባይቻልም ከተጠርጣሪዎቹ ከ1/3 በታች የሚሆኑት ላይ በጣቢያና በማረሚያ ቤት የጊዜ ቀጠሮ ተጠይቋል፡፡
10. የወንጀል ምርመራ ሥራ ከሌሎች የፍትህ አካለት ጋር ተቀናጅቶ በማሰረቱ ለአብነት የሚጠቀሱ ተሞክሮዎች ካሉ ይገለጽ
   - ከበድ ያሉ የብሔረሰብ ግጭት ወንጀሎች ስፈፀሙ ከፍትህ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራት ያለ ቀጠሮ ውሳኔ የሚሰጥበት ሥራዎች ተሰርቷል፡፡

   ለምሳሌ የሐመር, የዳሰነች ገዳዮች ፡ የዳሰነች,ሐመር ገዳዮች ፡ የዳሰነች ቦረና ገዳዮች ነፍስ ግድያ፣ጠለፋ፣አስገድዶ መድፈርና ያለ ዕድሜ ጋብቻ በቅንጅት ከሚሠሩት መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ (በበናጸማይ ወረዳ)

CAPACITY

11. ለፖሊስ ከቀረቡት የክስ ጉዳዮች መካከል ምን ያህል የምርመራ መዝገብ በሰዓታት በቀናትና በወራት ለሚመለከተው ተላልፏል-----------ሳይተላለፉ የቀሩ ጉዳዮች ምን ያህል ናቸው ምክንያታቸውን--

- እግዝብቶች ከጂንካ ከተማ አስ/ ፖሊስ ውጪ ባሉ ወረዳዎችና በዞኑ የሚቀመጡት በፖሊስ እጅ ሳይሆን በፍ/ቤት በመሆኑ ፖሊስ ምርመራውን ስያጠናቀቅ ለፍ/ቤት የሚያቀርብ በመሆኑ ለአፈጻጸሙ ምላሽ የሚገኘው ከፍ/ቤቶች ነው፡፡

12. በፖሊስ በእግዚቢት የተያዙ ንብረቶች ደህንነታቸው ተጠብቆ በፍጥነት ለባለንብረቱ እንዲመለስ በተቀመጠ አሠራር ምን ያህል ለባለንብረት ተመልሷል በገንዘብ-------ያልተመለሰ ንብረት በገንዘብ ሲተመን

-

13. ከBPR አተገባበር አንጻር የተገኘ ውጤት ያጋጠማቸው ችግር እንዲሁም ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች ተለይተው ቢቀመጥ

- የወንጀል ቁጥር በአንዳንድ ወረዳዎች መቀነስ
- ህ/ቡ በወንጀል መከላከል ሥራ በባላቤትነት ውሳኔ ሰጭ መሆኑ
- የህ/ብ ደህንነት መከበርና የብሔረሰቦች ግጭቶች መቀነስ
- አባላት ግንዛቤ ጥሩ መሆኑ
- የፖሊስ አደረጃጀት ለህ/ቡ ተደራሽ መሆኑ
- ህ/ቡ ከፖሊስ ጎን ሆኖ በመሥራቱና የራሱን ቀበሌ/ቀጠና/ እራሱ በመጠበቅ በመቻሉ ወንጀል ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ቀንሷል፡፡
- ከዚህም በተጨማሪ የጥበቃ ጓዶችና ህዝቡ ወንጀለኞችን ይዘው ወደየጣቢያው በመምጣት ለፖሊስ በማስረከብ ላይ ይገኛል፡፡

<u>ያጋጠሙ ችግሮች</u>

- የግንዛቤ ማነስ መኖር
- የሰው ኃይል እጥረት በመኖሩ ቀበሌዎችን በበቂ የፖሊስ ኃይል ማደረስ ያለመቻል፡፡

<u>ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች</u>

- የግንዛቤ እጥረቱን ለመቅረፍ አቅም ያለው በማኑዋሉ መሠረት በየቀበሌው የሚመደቡ የቀበሌ አፊሰር የቀበሌ ፎካል ፐርሰን የቀበሌ ማህበራዊ አገልግሎት ኃላፊ የሚሟሉበት መንገድ በቀጣይ በሚመለከታቸው መመቻቸት ይኖርበታል፡፡
- የመመርመርና መክሰስ ንዑስ የሥራ ሂደት በቀበሌ ደረጃ ወይም በአማካይ ቀበሌዎች ድረስ መዋቅሩ አለመውረድ የህ/ሰቡ መጉላላት የሚያመጣ በመሆኑ አደረጃጀቱ መሻሻል ይጠይቃልና ፈጣን ምላሽ ይሻል፡፡

## <u>ማረሚያ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራምን በተመለከተ</u>

CAPACITY

1. የታራሚዎችን ሰብአዊ መብት ከመጠበቅ አኳያ ስታንዳርድ የጠበቀ የእስረኞች ማደሪያ ተለይቶ በየማረሚያ ቤት ቢቀመጥ
   - ❖ ስታንዳርድ የጠበቀ የእስረኛ ማደሪያ የለም ነገሪ ግን ከአጭሪ ጣሪያና ከጠባብ ግርግዳ የተሰሩ ቤቶች ታራሚዎች ለሙቀት እና ለጠና ችግር በቀላሉ ይጋለጡ ነበረ፡፡አሁን ግን እነዚህን በማፍረስ የታራሚዎች ሰበዓዊ መብት ከመጠበቅ አንጻር ጣሪያዎችን ሰፋ አድርጎ በመሥራት የማደሪ ችግራቸውን ባለው ውስን በጀት ተጠቅሞ እየተሰራበት መሆኑ
2. አስረኞች በዕድሜ በጾታና በወንጀላቸው ክብደትና ቅለትተለይተው የሚያዙበት ሁኔታ የማረሚያ ቤት ተዘርግቷል ወይ ከልተዘረጋ ምክንያቱን
   - ❖ እስረኞችን በጾታ በወንጀላቸው ክብደትና ቅለት እንዲሁም የቀጠሮና ፍርደኛ እስረኛዎችን እንዲታሰሩ ተደረጓል፡፡
3. የማረሚያ ቤቶች የመና አቅርቦትና ግዥ ግልጸኝነትን የተከተለ እንደዲሆን በየማረሚያ ቤቶች ሁኔታዉን ለማስተካከል በተዘረጋ ሥርዓት የተገኘ ለውጥ ቢገለጽ
   - ❖ ለህግ ታራሚዎች መና አቅርቦት ግልጽ የሆነ ጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ተጫራቾችን በተቋሙ የጨረታ ኮሚቴና ከህግ ታራሚዎች በተቋቋሙ የታራሚ ጨረታ ኮሚቴዎች ጋር በመሆን ግልጽ በሆነ መንገድ በግዥ እየተፈጸመ ይገኛል፡፡
   - ❖ ታራሚውም ከመ/ቤቱ ጋር የምሰሩትን የራሱን ኮሚቴ በመምረጥ የተመደበለትን በጀት በትክክል እየተጠቀመ  ይገኛል፡፡
4. የታራሚዎች መና የተመጣጠነ ለማድረግ አቀራረቡ ደረጃውን እንዲጠብቅ ለማድረግ የተደረገ ጥረት
   - ❖ የመና እህልና ቅመማቅመም አቅራብ ነጋዴዎች ደረጃውንና ጥራቱን የጠበቀ መና እንዲያቀርቡ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርጉ ከመ/ቤቱ አባል 3 ከህግ ታራሚ 3 በድምሩ 6 የጥራት ቁጥጥር ኮሚቴ በማቋቋም ክትትል ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ታራሚዎች በወር አንድ ጊዜ ሥጋ እንድመገቡ ተደርጓል፡፡የእርድ በሬ ግዢ የሚፈመው ከሕግ ታራሚ ከተመረጡ ኮሚቴዎች ጋር በመሆን ነው፡፡
5. የታራሚዎች የሕክምና አሰጣጥ፣በባለሙያ አመዳደብ፣በመድኃኒት አቅርቦትና የህክምና መረጃ መሳሪያዎች አደረጃጀት በየማረሚያ ቤት እንዲኖር ለማድረግ በተዘረጋ ሥርዓት የተገኘ ለውጥ ቢገለጽ
   - ❖ ለህግ ታራሚዎችና ለመ/ቤቱ አባሎች ህክምና አገልግሎት የምሰጥ መለስተኛ ክሊኒክ ተቋቁሞአል፡፡ሁለት የህክምና ባለሙያዎችን በመቅጠር አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ መድኃኒት ግዥ ግልጽ በሆነ አኳኋን እየተፈጸመ እየተሠራበት ነው፡፡ህክምና በመስጠትና ከአቅም በላይ ሲሆን ለጂንካ ዞናል ሆ/ል በሪፈር በመላክ በመንግስት ወጪ እንዲታከሙ ተደርጓል፡፡
6. ፍርድ የተፈረደባቸው እስረኞች ወደፊት ህግ አክባሪ እንዲሆኑ የተሰጠ የትምህርት ዓይነት የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና የተሳታፊ እስረኞች ብዛት በሙያና በጾታ ተለይቶ ቢገለጽ

CAPACITY

- ❖ የህግ ታራሚዎች ወደፍት እስራቸውን /ፍርዳቸውን/ጨርሰው የህብረተሰቡ አባል ይሆናል፡፡ስለዚህ በእስር ቤት ቆይታቸው የወንጀል አስከፍነት ምክርና ትምህርት እየተሰጠ ይገኛል፡፡በተጨማሪም የቀለም ትምህርት ከጂንካ ከተማ አስተዳደር አ/ግ/ማ/ጽ/ቤት ጋር በመተባበር 1-4ኛ ክፍል በመክፈት መደበኛ ት/ት እየተሰጠ ሲሆን ወንድ 152 ሴት 12 በድምር 164 ታራሚዎች የዕድሉ ተጠቃም ሆነዋል፡፡ታራሚዎች የእስር ጊዜያቸውን ጨርሰው ሲወጡ በህብረተሰቡ መሃከል ሲኖሩ የላቸውን ለውጥ ለመጋምገም የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ከሆነ ቢገለጽ

7. የለም
8. የክልሉ መንግስት በተለያዩ ጊዜ በምህረት፣በአማክሮና በሌሎች ምክንያቶች እስረኞች እንዲለቀቁ ያደርጋል ስለሆነም ማረሚያ ቤቶች ለዚህ ሁኔታ እስረኞችን በፀባይ ያሳዩትን ማሻሻያ በየጊዜ ለይቶ የማስቀመጥ አሠራር ሁኔታ በዝርዝር ቢቀመጥ
   - ❖ የህግ ታራሚዎች ለህግ-መንግስቱ ተገዥና የተቋሙን መመሪያና ደንብ አክባር እንዲሁም መልካም ስነ-ምግባር የተላበሱና በህግ የበላይነት የምያምን ዜጋ ሆነው ታንጸውና ታርምው እንዲውጡ የታራምውን እንቅስቃሴ በየጊዜው ክትትልና ግምግማ ይደረጋል፡፡በየጎሳ አሰባስቦ ኮሚቴ በማዋቀር የእርስ በእርስ የጎሳ ግጭት እንዳይነሣ የምመክሩና የምደኙ በተለይ ከአርብቶ አደር አካባቢ የምገቡ ታራሚዎች የግንዛዜ ለውጥ እንዲያመቱ ለማድረግና በጋራ በፍቅርና በአንድነት የመኖር ባህል አዳብረው እንዲወጡ ጥረት እየተደረገ ሲሆን ለህግ ተገዥ የማይሆንና በህግ የበላይነት የማያምን ምግባረ ብልሹ ታራሚዎችን እንዲሁም ተመላላሽ ታራሚዎችን ለብቻ በመለየት በአመክሮ ኮሚቴ ጉዳያቸውን በማጣራት ውሳኔ እየተሰጠና የአመክሮ ዕድል እየተነፈጉ ይገኛል፡፡
9. ከBPR አተገባበር አንጻር የተገኘ ውቴት ያጋጠማቸው ችግር እንዲሁም ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች ተለይተው ቢቀመጥ
   - ❖ BPR አተገባበርን በተመለከተ ተቃማችን የሙከራ ጊዜውን ጨርሶ ወደ ሙሉ ትግበራ ከገቡ ሰክተር መ/ቤቶች አንዱ ሲሆን በፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት አሰጠጥ ደንበኞችን/ባለጉዳይን/ እያረካ ያለ ስለመሆኑ ከበርካታ ተገልጋይ አስተያየት በማሰበሰብ ተገንዝበናል በተጨማርም ተቋሙ 3 የሥራ ሂደቶችን ያቀፈ ሲሆን በተለይ በማረምና ማነጽ ዋና የሥራ ሂደት የቲሙ አባላት የቲም ቻርተር ተፈራርሞ ስራውን እያከናወነ ያለ ከመሆኑም በላይ በሳጥን በመዝገብና በቅጽ ከተገልጋይ አስተያየት በማሰባሰብ በእየዕለቱ አገልግሎት መከታተያ ቅጽ ላይ የእለት ክንውኑን እየሞሉ
10. በማረሚያ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም አፈጻጸም ሌሎች ያልተጠቀሱ ስራዎች ተሰርተው ከሆነና በሥራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች በዝርዝር ይገለጽ

    ስራውን በፈጣንና ቀልጣፋ ሁኔታ እያከናውኔ አበረታች ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

CAPACITY

CAPACITY

## II. የኢኮቴ መሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት የስራ ሂደት በተመለከተ፡-

የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ማስፋፋትና በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ለ80 ሠልጣኞች መሠረታዊ የኮምፒውተር ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ100 ሠልጣኞች ተሠጥቷል ።

የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሳሪያዎች በዞንና ወረዳ በመገኘት ጥገና በማድረግ 16,800 ብር ልያወጣ የሚችል ወጪ ማዳን ከመቻሉም በተጨማሪ ለጥገና ወደ ክልል የሚደረግ ጉዞና ወጪ ለማስቀረት ተችሏል።

መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ የተገበሩ የሥራ ሂደቶችን ኮፒውቲራዝ ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሠረት 10 ኮምፒውተር እና 30 እስካነሮች በዞን በ8 ወረዳዎችና ጂንካ ከተማ አስተዳደር ተሰራጭቷል። የኢኮቴ መሳሪያዎች ፍላጎት ለማወቅ በተደረገዉ የዳሰሳ ጥናት በዞን መ/ቤቶች

ኮምፒውተር 109፤ላፕቶፕ 51፤ፕሪንተር 76፤ፎቶ ኮፒ 26፤ፋክስ 28እና ስካነርስ 30 ፍላጎት መኖሩን እንዲሁም በ8ቱ ወረዳና ጂንካ ከተማ አስተዳደር ኮምፒውተር 252፤ላፕቶፕ 100 ፤ ፕሪንተር 225 ፤ፎቶ ኮፒ 189 ፤ፋክስ 135 እና ስካነርስ 90 ፍላጎት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡የኢኮቴ መሣሪያዎች ባለመሟላታቸዉ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ተግባራዊ ያደረጉ የዞንና ወረዳ መ/ቤቶች በአሠራር የስታንዳርድ መሠረት ሥራዎች እንዳያከናወኑ ቀላል የማይባል ተፅእኖ ልኖረዉ ስለሚችል በቀጣይ ትኩረት ልሰጥ ይገባል፡፡

ቀበሌያትን የዘመናዊ መረጃ ልውውጥ ስርዓት ተጠቃሚ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት 70 ቀበሌያት የሽቦ አልባ ስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ከክልል አቅም ግንባታ በተገኘ ድጋፍ በሐመር ወረዳ እና በዞን የመረጃ ማዕከል ተቋቁሞ ነፃ የመረጃ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ተጨማሪ የመረጃ ማዕከል በዳሰነች እና ጂንካ ከተማ ለማቋቋም ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

CAPACITY

## III.የሰዉ ሀብት ልማት የሥራ ሂደት በተመለከተ፡-

በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ/BPR/ ጽንሰ ሀሳብ፤በለዉጥ አመራር፣በማስፈፀም አቅም ግንባታ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ወዘተ ላይ በዞን ሴክተር መ/ቤቶች፣በ8ቱ ወረዳና ከተማ አስተዳደር ለ4,306 አመራርና ሰራተኞች ፤ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ5,572 ስልጠና በመስጠት ጥናቱ የተጠናቀቀላቸ ሰባት ሰክተር መ/ቤቶች በሠላሣ አንድ ዋና እና ሶስት ደጋፊ በድምሩ ሠላሣ አራት የሥራ ሂደቶች

ወደ ሙሉ ትግበራ እንዲገቡ ሲደረግ በከተማና በገጠር ከ108 ቀበሌያት 103 ከተቀጠሩ ሥራ አሥኪያጆች ዉስጥ ለ100 ስልጠና በመስጠት የመንግስት መዋቅር በቀበሌያት ተዘርግቷል፡፡

የሰለጠነ የሰዉ ኃይል ክፍተት ዳሰሳ ጥናት ለማድረግ በታቀደዉ መሰረት ደጋፊ የስራ ሂደቶችን ብቻ የተገበሩ መ/ቤቶችን ሳይጨምር በዞን መምሪያዎች፣ በወረዳና በጂንካ ከተማ 375 የሥራ ሂደቶች ዉስጥ የሰዉ ኃይል ያልተመደበበት 158(42.32%)፤ 1እስከ74% ድረስ የሰዉ ኃይል የተመደበበት 116(30.93)፤75% እና በላይ የሰዉ ኃይል የተመደበበት 101(26.93) ሲሆን በሥራ ሂደቶች ላይ

ከሚያስፈልግ 1363 የሰዉ ኃይል የተመደበ 438(32.13%)፣ ክፍት መደብ 925(67.7%) ነዉ። ከክፍት መደቦች የመጀመሪያ ዲግርና በላይ የሚጠየቀዉ 187(20.22%) ዲግር ወይም ዲፕሎማ የትምህርት ደረጃ የሚጠይቁ መደቦች 738(79.78%) ይሆናል:: እስከ75% የሰዉ ሀይል ያልተሟላባቸዉ 274 የሥራ ሂዶቶች 582 የሰዉ ሀይልና ለአንድ ወር ደመወዝ የበጀት መጠን

ብር695,114.00 ሚያስፈልግ መሆኑ በጥናት ተረጋግጧል።75% የሰዉ ሀይል ለመማሟላት ከሚያስፈልገን 582 ዉስጥ 188(32.30%) በተፈጥሮ(የእፀዋትረና እና የእንሰሳት) ሣይንስ ፣ 179(30.75%)በኢኮኖሚክስ፤በማናጅመንት፤ በአካዉትግና በተዛማጅ የሙያ ዘርፎች፣144(24.74%) ማህበራዊ፣ተፈጥሮ ሳይንስ፣በማስተማር እና ጂኦግራፊ፣ፖለቲካል ሳይንስ፣ማነጅመንት፣በህግ፣ ሶስዮለጂ እና ተዛማጅ፣71(19.20%)የስቪል፣የህንፃ፣የከተማ ምህንድስና፤ቅየሳ፤የከተማ ፕላንና ወዘተ የሙያ መስመር ላይ ያተኮረ በመሆኑ የሰዉ ሀብት የማሟላት ሂደት ላይ ለተጠቀሱት የሙያ መስመሮች ቅድሚ ያተሰጥ እንዲሰራ ተደርጓል።

የአቅም ግንባታ የስራ ሂደት ለዞን መምሪያዎች፣ለጂንካ ከተማና ለወረዳዎች ዕቅድና የአፈጻጸም ስምምነት ሰነድ፣ ተዘጋጅቶ ተልኳል። በአዲሱ ሥራ ሂደት አተገባበር ላይ በቼክ ልስት ድጋፍ፣ ምክርና እገዛ ተደርጓል። በህግ ሙያ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ በተያዘው ዕቅድ መሠረት ከአርብቶ አደር አከባብዎች 50 ዕጩ ሰልጣኞች ተመልምለዉ ለረጅም ጊዜ ስለጠና እንዲገቡ ተደርጓል። የሰው ሃብትን ከማብቃት አንጻር 91 ባለሙያዎች ለመጀመሪያ ዲግሪ ፣ 4 ባለሙያ ለሁለተኛ ዲግሪ በድምሩ 95 ባለሙያዎች ለረጅም ጊዜ ስልጠና በመደበኛና በተልዕኮ ተወዳድረዉ ዉጤታቸዉን እየተጠባበቁ ይገኛሉ ።

## <u>በሰው ሃብት ሥራ አመራር የሥራ ሂደት</u>

- በሰሜን አሪ ወረዳ በግብርና ጽ/ቤት፤በፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት፤በአቅም ግንባታ ጽ/ቤት ከBPR በፊት በታህሳስ ወር 2001 በተደረገው የእንስፔሽን ሥራ 19112.00 ብር ያለአግባብ ለደረጃ እድገት የተከፈለው ተመላሽ እንዲሆን ተደርጓል።
- ከዞን መመሪያዎች፣ከጂንካ ከተማ አስተዳደር እና ከ8ቱ ወረዳዎች የቀረቡ 48 አቤቱታዎች በቂ ምላሽ አግኝቷል።
- ከ8 ወረዳ እና ከዞን አቅም ግንባታ የተፈጸመ ቅጥሮች በዞን ተመዝግቦ ለክልሉ አቅም ግንባታ ተላልፏል።
- የሠራተኞች ጥቅማጥቅም አከባበር በተመለከተ የድጋፍ ደብዳቤ፤የዓመት ፍቃድ፤ ክልራንስ እና የተለያዩ ጥቅማጥቅሞች በስታንዳርዱ መሠረት አገልግሎት ተሰጥቷል።

CAPACITY

- የሰው ሃብት ሥራ አመራር ማኑዋል ላይ ለዞንና ወረዳ የሰው ሃብት ሥራ አመራር የሥራ ሂደት ባለሙያዎች ሥልጠና ተሰጥቶ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡

- በ8 ወረዳ እና በዞን 6 መምሪያዎች መሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ ሙሉ ትግበራውን ለማስተባበር ለሰው ሃብት ሥራ አመራር የስራ ሂደት ድጋፍና ክትትል በግንባር ተሰጥቷል፡፡

- ከጥር1-ሴኔ 30/2001 በመሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ የ6 ወር ዕቅድ መርሃ ግብር እና ቲም ቻርተር ተዘጋጅቶ ተግበራዊ ተደርጓል፡፡

CAPACITY